# <u>ከኑረንበርግ ኢትዮጵያውያን ባሕል ማህበር (ኮሚኒቲ) በወቅታዊ አገራዊና ኮሚኒቲ ነክ ጉዳዮች ዙሪያ የኮሚኒቲውን አቋም በተመለከተ ለኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናትና ተቋማት፣ በጀርመን ለኢትዮጵያ መንግስት ተወካዮች፣ ለዓባላትና እንዲሁም ደጋፊዎች ትክክለኛ ግንዛቤ ማስያዝን አላማው ያደረገ መግለጫ</u>

ውድ የማህበራችን ዓባላት፣ በኑረንበርግና አካባቢው ነዋሪ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም የኢትዮጵያ ወዳጆች ሆይ!

ብዙዎቻችሁ እንደምታውቁት የኑረንበርግ ኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ ከ እኤአ 1990 ዓም ጀምሮ ላለፉት 32 ዓመታት ከየትኛውም የዘር፣ የሃይማኖት ወይንም የፖለቲካ አስተሳሰብ አራማጅ ቡድን ሳይወግን ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በሚያግባቡን ጉዳዮች ዙሪያ ብቻ ለማሰባሰብ ሲሰራ የቆየ፣ በከተማችን ባሁኑ ዘመን ትልቅ ሆነው የሚገኙትን እንደ ዕምነት ቤቶችና እደር የመሳሠሉ ማህበረሰባዊ አደረጃጀቶች ቆርቋሪ የሆነና ጀርመን ላይ አሉ ከሚባሉ አንጋፋና በዓላማ የጸኑ ኮሚኒቲዎች ዋነኛው ነው ብንል ማጋነን አይሆንም። ይህ አንጋፋ ማህበር መሠረቱን ኢትዮጵያዊነት በማድረጉ በህወሃትኢህአዴግ  የአገዛዝ ዘመን እንደ ተፎካካሪ ሓሳብ አራማጅ ሥብሥብ ሳይሆን እንደ ጠላት ሲታይና ዓባላቱም ዋጋ ሲከፍሉ እንደኖሩ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በ 2018 ዓም ላይ በአገራችን በተከሰተው ፖለቲካዊ ለውጥና ይህንንም ተከትሎ በተከሰተው የኢትዮጵያዊነት ማንሠራራት ትልቅ ተሥፋ በመሠነቅ ባለው አቅም ሁሉ ይህንን የለውጥ ሃይል በመደገፍ ትንሳኤአችንን እውን ለማድረግ የሚደረገውን ርብርቦሽ በተግባር በመቀላቀል በለውጡ ሂደት ውስጥ በተፈጠሩ ግጭቶችና ጦርነቶች ሳቢያ ለተጎዱ ወገኖች ድጋፍ በማቅረብ፣ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን በዘላቂነት የሚጠቅሙ ፕሮጀክቶችን በመደገፍና የአገራችን ጠላቶች የከፈቱትን የፕሮፓጋንዳ ጦርነት በማምከን ዙሪያ የሚሠሩ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራዎች ላይ በንቃት በመሳተፍ አስተዋጾ ሲያደርግ ቆይቷል።
ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ታይቶ በማይታወቅ መልክ ኢትዮጵያውያን ቅጥረኞቻቸውን በመጠቀም በጥልቀትና በስፋት ያተኮሩበትን ሕዝብን ከሕዝብ የማናከስ ዘመቻ ተከትሎ በተለይ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ውስጥ በንጹሃን ወገኖቻችን ላይ የተፈጸሙ የግፍ ጅምላ ግድያዎችንና ይህም በብዙ ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን ዘንድ የፈጠረውን ምሬት እንደ መልካም አጋጣሚ በመውሰድ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስብስቦችን እጅ ጠምዝዞ ለግል የፖለቲካ ዓመለካከት መጠቀሚያ ለማድረግ እንቅስቃሴው በርትቷል። ለዚህም በተራ ሐሰት የግለሠቦችን ሥም ማጥፋት፣ ማህበራትን በሃሰት የዚህ ወይንም የዚያ ፖለቲካ ዓመለካከት ተለጣፊ አድርጎ ማቅረብ፣ ሠላማዊና አገር ወዳድ ወገኖችን  ከኢትዮጵያዊ ጨዋነት ወጣ ባለ መልኩ መዝለፍ በአሳዛኝ ሁኔታ ተጧጡፈዋል። ይህ ኢትዮጵያዊነትን ማዕከል አድርገው የተሠባሠቡ ወገኖች እርስ በርስ በጥርጣሬ እንዲተያዩና አንድነታቸው እንዲላላ ምክንያት የመሆን ዕምቅ አቅም ያለው አደጋ ነው። የትናንሾቹ ኢትዮጵያውያን ስብስቦች መዳከም የትልቋ ኢትዮጵያ መዳከም ነው።

ስለሆነም ማህበራችን ከላይ ባነሳናቸው ጉዳዮች ዙሪያ ያለውን አቋም በድጋሚ በየዘርፉ ላሉት ባለድርሻ አካላት እንደሚከተለው ለማሳወቅ እንወዳለን።

1. **የንፁሃንን ጅምላ ጭፍጨፋ በተመለከተ በጀርመን ለኢፌዲሪ አምባሳደር፣ ለጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ፣ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ለክልል መስተዳደሮችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሌሎች የመንግስት አካላት**

በኢትዮጵያ በክልሎች በተለይም በኦሮሚያ ክልል በዜጎች ላይ እየተፈጸሙ ያሉ ዘር ተኮር ጭፍጨፋዎችን አጥብቀን እናወግዛለን! በዚህ ክልል በተደጋጋሚ እየተፈፀሙ ያሉ መሠል የሽብር ድርጊቶች መንግስት ውስጥ በመሸጉና ከመንግስት ውጭ ባሉ የተደራጁ ሃይሎች በመናበብ የሚፈፀሙ ኢሰባዓዊ ወንጀሎች መሆናቸውን የሚያመላክቱ አያሌ መረጃዎች አሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ በሌሎች ክልሎች በኦሮሚያ ክልል ከተፈጠሩት ችግሮች በእጅጉ ላነሱ አደጋዎች የተሠጡትን ዓይነት የክልል ርዕሠ መስተዳደሮችን ሳይቀር መቀየርን የሚያካትቱ ፈጣንና ቆራጥ ማስተካከያ እርምጃዎች ለመውሠድ ማዕከላዊ መንግስቱ ለምን ተሳነው? የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ያለ አግባብ በግፍ መገደል የኢትዮጵያዊነትና የኢትዮጵያ ትንሽ ትንሽ ሞት አይደለም ወይ? የኦሮሚያ ክልል በዚህ ደረጃ ለሰባዓዊነትና ለአገር ህልውና ደንታ ቢስ ጉልበተኞች መፈንጫ እንዴት ሊሆን ቻለ? በአንድ የማህበረሠብ ክፍል ሞትና ስቃይ ላይ (ለዚያውም ከሕዝቧ ብዛት በግምት 35%ቱን የሚይዘውንና በአገረ መንግስቷ አፈጣጠር ላይ ትልቅ አሻራ ያለውን የአማራ ሕዝብ) የምትቆም ኢትዮጵያ ልትኖር ትችላለችን? የሚሉ ጥያቄዎች በአእምሮአችን ይመላለሳሉ። መንግስት የመረጠውን ሕዝብ አካላዊና ቁሳዊ ደህንነት የመጠበቅ ዋነኛ ተልዕኮውን በአግባቡ ይወጣ ዘንድ፣ አውቀውም ሆነ በብቃት ማነስ የንጹሃንን መጨፍጨፍ መታደግ ያልቻሉ ባለስልጣናትን ያለምንም ማወላዳት ህግ ፊት አቅርቦ ሕዝብ የሚጠብቀውን ፍትህ እውን ያደርግ ዘንድ አበክረን እንጠይቃለን! ይህንን ግዴታውን እንዳይወጣ ከሚያደርጉ የውስጥ አርበኞች እራሱን ማጽዳት ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ ጉዳይ ነው ብለን እናምናለን!

2. **የዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን ስብሰቦችን ላይ የራስ ዓመለካከትን ለመጫን እየተካሄደ ያለውን ዘመቻ በተመለከተ ለአባላቶቻችን እና በከተማችን ነዋሪ ለሆናችሁ ኢትዮጵያውያን**

ከላይ በዚህ ጽሁፍ መጀመሪያ ላይ እንዳስታወስናችሁ የማህበራችን መፈጠር ምክንያት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ናቸው። የምናዝነው በኢትዮጵያውያን ሃዘን፣ ስንጮህ የነበረው ለኢትዮጵያውያን በደል፣የምንደሰተው በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ስኬት ነው። እድሜ ዘመናችንን ለዚህ ዓመለካከት ታምነን የቆየን ሠዎች በአሥራአንደኛው ሠዓት ላይ የጠላቶቻችን ወጥመድ የሆነው የዘር ፖለቲካ አቀንቃኝ የምንሆንበት ምንም ምክንያት አይኖርም። በየትኛውም ክልል ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ያለአግባብ በደል ሲደርስባቸው እራሳችን ላይ እንደደረሰ በደል እንወስደዋለን። ያለማቅማማትም እናወግዘዋለን። ሃላፊነት ያለባቸው የመንግስት አካላት በአፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ እንወተውታለን።

ህወሃት በአገዛዝ ዘመኑ በምዕራባውያን ሙሉ ድጋፍ በጠብመንጃ የመንግስት ሥልጣንን ተቆጣጥሮ

በነሱው ሞግዚትነት በኢትዮጵያውያን ላይ ከባድ በደል ሲፈጽም ስለነበር በናንተ ያላሠለሠ ድጋፍ ሕዝባችን እየተበደለ ነው ስለዚህ ጭፍን ድጋፋችሁን መርምሩ እያልን በአደባባይ ጠይቀናል። ዛሬ ላይ ሁኔታዎች ተለውጠዋል። ሕዝባችን ባደረገው የሞት ሽረት ትግል የህወሃትን አምባበገነናዊ ሥራዓት አውርዶ በዛም አነሰ ይሆነኛል ያለውን መንግስት መርጧል። በዚህ መንግስት ደካማ ጎን ምክንያት ሕዝብ ላይ ለሚደርሱ በደሎች ድምጻችንን ከፍ አድርገን የምንጮኀው ወደራሱና ወደወከለው ሕዝብ ይሆናል። ከሶስት ዓሥርት ዓመታት በላይ ያካበትነው የህይወት ተሞክሮ ካስተማረን ነገሮች አንዱ የኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ችግሮች በዘላቂነት የሚፈቱት በራሳችን ኢትዮጵያውያን ብቻ መሆኑን ነው። ዘርን መሠረት የሚያደርጉ አደረጃጀቶችን በተመለከተ ባለፉት 30 ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ በተደራጀና በመንግስት መዋቅራዊ ሙሉ አቅም ሆን ተብሎ በሕዝባችን ውስጥ የተተከለው በዚሁ በዘር ፖለቲካ የታጠረ አስተሳሰብ መሆኑን እንረዳለን። በአስርት ሚሊዮን የሚቆጠሩ ወጣቶቻችን ያደጉበት ፖለቲካዊ አስተሳሰብና አደረጃጀት መሆኑ መሬት ላይ ያለ ሃቅ ነው። ዓላማቸው በኢትዮጵያ ምድር ላይ ፍትህንና ዕኩልነትን ማስፈን እስከሆነ ድረስ በተለያዩ መንገዶች ብንጓዝም መዳረሻችን አንድ ቦታ ነው ብለን እናምናለን። ስለሆነም ያዋጣናል ባሉት መንገድ ተደራጅተው ለመብታቸው መከበር ለሚያደርጉት ትግል ዕውቅናና አክብሮት እንሰጣለን። እነዚህ ወንድምና እህቶች ሊገነዘቡትና ሊቀበሉት የሚገባው ወሳኝ ጉዳይ ኢትዮጵያን የሚጋሩት ከሌሎች ብሄር ፖለቲካ ዓራማጆች ጋር በቻ ሳይሆን ራሱን ከዚህ ወይንም ከዚያ ብሄር ጎራ ለመመደብ ሥነልቦናዊም ሆነ አይምሮዓዊ አወቃቀሩ የማይፈቅድለት በኢትዮጵያዊነት ብቻ የታነጸ ቁጥሩ አያሌ ሚሊዮን ከሚገመት ዜጋ ጋርም መሆኑን ነው። በመሠረቱ አደረጃጀቶቹ የግድ መቃረን የለባቸውም። ችግር የሚፈጥረው አንዳንዶች አሁን አሁን ሲያሰሙት የሚስተዋለው እንደኛ ካላሰባችሁ ጠላቶቻችን ናችሁና ምክንያት እየፈለግን ከናንተ ጋር አምባጓሮ እንፈጥራለን የሚለው ደካማ ፈሊጥ ነው። ይህን እያደረጉ ያሉ ወገኖችን በሁለት ከፍለን እናያቸዋለን። አንደኞቹ ቀደም ሲል እንደጠቀስነው የራሳቸውን የፖለቲካ ዓመለካከት በግድ ሌሎች ላይ ለመጫን የሚጥሩት ሲሆኑ ሁለተኞቹ ደግሞ በግለሰብ ደረጃ ያላቸውን ስሜት ከማህበረሰባዊና አገራዊ ኩነቶች አኳያ ገምግሞ መግራት የተቸገሩና ለመጀመሪያዎቹ ባለተልዕኮዎች አጀንዳ ምቹ ሆነው ኢትዮጵያውያን እንዴት ማሠብ እንዳለባቸው ትዕዛዝ የመስጠትን ፍላጎት እያገዙ የሚገኙት ወገኖች ናቸው። ይህንን ኢዲሞክራሲያዊ አካሄድ ማስተካከል የምንችለው እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ስብስብ ዓባላቱም ሆነ ማህበረሰቡ ስለ መሠል አጀንዳዎች አንደምታ ከጅምሩ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲይዝ በማድረግ የግል ህመሞቻችንንና የተጎዱ ስሜቶቻችን ለአሣሣቾች መጠቀሚያ እንዳያደርጉን ከፍተኛ ጥንቃቄ መውሰድ እንድንችል ሲያደርግ ይሆናል። የአገር ሠላም የሚጀምረው ከኛው ሠላምና አንድ ሆኖ መቆም ነውና ሁላችንም ችላ ሳንል ለሠላማችንና አብሮነታችን በያለንበት ዘብ እንቁም!

ብቸኛ መዳኛችን ኢትዮጵያዊነት አሸናፊ ነው!

ከአክብሮት ሠላምታ ጋር

የኑረንበርግ ኢትዮጵያውያን ባህል ማህበር

ሥራ ዓመራር